# ያግኙን

በሚከተለው ዋና ገጽ www.amnesty.org ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል መገናኘት ይችላሉ።

**Amnesty International**
**International Secretariat**
**Peter Benenson House**
**1 Easton Street**
**London WC1X 0DW**
**United Kingdom**
**Phone: +44 (0)20 7413 5500**
**Fax: +44 (0)20 7956 1157**
**Email: amnestyis@amnesty.org**

# ታሪክዎን
# ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ቢያካፍሉስ

## በአንድ ላይ ሆነን ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት እንችላለን

## እኛ ማን ነን?

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ከ150 አገሮች በላይ በሚኖሩ፣ ቁጥራቸውም ከሁለት ሚልዮን ላቅ ያለ ሕዝቦች የሚካሄድና፣ ለሰብአዊ መብቶች የሚጣበቅ ዓለም አቀፋዊ ንቅናቄ ነው። ለፍትኅናና ለእኩልነት ጸንተን የቆምን ስለሆን፣ ማነኛውንም አይነት አድልዎ በጥብቅ እንቃወማለን። እንዲሁም፣ መንግስትና ሓያላን ቡዱኖች ህዝብ ተከብሮ እንዲኖር ይፈቅዱለት ዘንድ እንገፋለን።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ከማነኛውም የመንግስት፣ የዐለም በጎአድራጎትም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ነጻ ነው። በተጨማሪ ማነኛውም ርእዮተዐለም፣ ሃይማኖት ወይ እምነት አንደግፍም። ሆኔታዎ ሁሉ በአለምአቀፍ በታወቀው የሰብአዊ መብቶች ሚዛን አይተን ምንም ሳናዳላ እንሠራለን።

ንቅናቄአችን ሌላው ሰው እንዲመቸው በልብ በሚሠሩ ሰዎች የቆመ ነው። ሥራቸውም፣ ስቓይ በደረሰባቸው ወይም የሰብአዊ መብቶች ሲሻር አይተው፣ ለወደፊቱ በድጋሚ እንዳይጎድል በማሰብ ሊለውጡት በሚታታሩ ሰዎች የተጀመረ ነው። እንግዲህ የምንጣበቅለትን ጉዳዮች ዋናው መሰረት፣ የወንዶች፣ የሴቶችና የልጆች ሓቀኛ የሕይወት ታሪኮች ናቸው።

## የሥራችን አገባብ

ሥራችንን የምንጀምረው የሚያጋጥሙትን እውነቶች ፈልገን በማጣራት ነው። ስለዚህ የምያውቁትን ብያካፍሉን፣ ሁኔታዎችን በጠቅላላ በተሻለ መንገድ ለማወቅ ስለሚረዳን፣ የምንወስነው ውሳኔ ውጤታማ ይሆናል።

ፍቃደኛ ቢሆኑ ደግሞ፣ ታሪክዎን ማለት በእርስዎና በቤተሰብዎ ላይ የደረሰ ሁኔታ፣ በመላ ዐለም የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ሰምተዉት እንዲማሩበት ይረዳ ነበር። የመንግስት ባለስልጣኖችና የማኅበረሰብእ አባሎች፣ ኣንዲሁም ቤተሰብዎ በሙሉ፣ ስለርስዎ ታሪክ ማንበብ በችላሉ ነበር። ስእልዎ ልናወጣሎት ብንፈቅድሎት ደግሞ፣ ብዙ ሰዎች ፊትዎን በወረቀትም ሆነ በኮምፑተር ሊያዩት በቻሉ ነበር።

እንግዲህ የሚያካፍሉን መመርያ፣ እኛ ከእርስዎ ጋር ተወያይተንበት፣ ይበጃል ብለን በተስማማንበት አገባብ ግብራዊ እርምጃ እንወስዳለን። ከዚያን ጊዜ በኃላ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሰብአዊ መብቶች ግኅሰት ደግሞ፣ ከበፊቱ ያነሱና የቀለሉ እንዲሆኑ በተስፋ እንሠራለን።

በአካል ያጋጠማቸው ወይም ሌሎችን ሲያጋጥም ባይናቸው የተመለከቱ የብዙ ሰዎች ታሪኽ መዝግበናል። ኣንዳንዶቹ፣ ያካፈሉንን ታሪክ፣ በይፋ እንዳይሰራጭባቸው ወይም መንነታቸው (ስም፣ ቦታ፣ ኣለተ ልደት፣ ወዘተ.) ሳንንገልጥ እንድናጋባው ይነግሩናል። እኛም ሁሉ ግዜ ፍላጎቶቻቸውን በሚገባ እናከብራለን። ብበፍቃዳቸው ከሆነ ግን ታሪኮቻቸውን በሚከተሉት አርእስቶች መልክ የጥብቅና ዜቤዎች እንገለገልባቸዋል።

ለምሳሌ፣

- ምናልባት ስለ ጉዳይዎ ለመንግሥት ልንነግርሎት እንችላለን። እነ የምናስረዳው አካል፣ ያገርዎትን መንግሥት ጭምር እና ሌሎች መንግሥታት ሊሆኑ ይችላሉ።

- ምናልባት ታሪክዎ በ ዘገባ መልክ በመጼሔት ሊታተም ወይ በኢንተርኔት ሊተላለፍ ይችላል። የታተሙ ታሪኮች ደግሞ፡ ለብዙ ጊዜ እየተሰራጩ ሊኖሩ ይችላሉ።

- ምናልባት'ም ጉዳይዎን ለጋዜጤኞች አስረድተው፡ ታሪክዎን በሚድያ ሊያወጡት ይችላሉ። ጋዜጠኛታትች ሊያናግርዎትና ስእልልዎን ሊወስዱ ይፈልጉ ይሆናሉ።

- ባልደረቦቻችንና ረዳቶቻችን ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስዱ እንጠይቃቸዋለን። ይኸውም ደብዳቤዎች ወደ መንግስት ጽሕፈት ቤት እንዲልኩና ሰላማዊ ሰልፎች እንድያደርጉም ጭምር ነው።

- ለተባበሩት መንግሥታት ነግረን ጉዳይዎን እንዲጣራሎት ለማድረግ እንችላለን።

ሆኖም የርስዎን ሁኔታ ወድያውኑ እናሻሽሎዋለን ብለን ቃል አንገባም። የሰባአዊ መብቶችን ግኅሰት ጨርሶ እንዲቆም ዐቅማችንን እስከፈቅደ ድረስ በታታሪነት እየሠራን፡ ጥፋቶኞቹን ወደ ፍርድ ቤት እናቀርባቸዋለን። ነገር ግን የገንዘብም ሆነ የሌላ እርዳት መስጠት አንችልም።

## መምረጥ ይችላሉ

ከርስዎ ሳንስማማ፡ ማለት ያለ ፈቃድዎ የነገሩንን መመርያዎች ይዘን የምናካሄደው እንቅስቃሴዎች የሉም።

**መምረጥ ይችላሉ** ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ቃለ መጠይቅ ማድረግ ይችላሉ። ከመወሰንዎ በፊት ግን በቂ መረጃ ይኖሮት ዘንድ ማነኛውም ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ። ሁሉም ሰብ ይህን በመሳሰሉ ሁኔታዎች በዘፈቀደ እንደማይናገሩ ይገባናል።

**መምረጥ ይችላሉ** ስለሚነግሩን ታሪክ ለሌላ ሰው እንድናካፍል ወይም እንዳናካፍል።

**መምረጥ ይችላሉ** ስምዎንና ሌሎች ማንነትዎን የሚገልጹ መረጃዎች፡ ለሌሎች ማሳወቅ ወይም ላለማሳወቅ።

**መምረጥ ይችላሉ** ፎቶግራፍ ይነሱ ወይም ላይነሱ። ኣንዲሁም ስዕልዎን በመጼሔት ይውጣ ወይም ኣይውጣ።

**መምረጥ ይችላሉ** ከኛ በሚዋዩበት ወቅት ደግሞ፡ መልስ የመስጠት ወይም ላለመስጠት። እንዲሁም ቃለመጠይቁን በፈለጉበት ጊዜ የማቆም ወይም ላለማቆም።

ለማነኛውም ነገር፡ የመረጡ ቢመርጡ፡ ግዜዎን ስለሰጡን በጣም እናመሰግኖታለን

**Amnesty International**
**International Secretariat**
**Peter Benenson House**
**1 Easton Street**
**London WC1X 0DW**
**United Kingdom**
**Phone: +44 (0)20 7413 5500**
**Fax: +44 (0)20 7956 1157**
**Email: amnestyis@amnesty.org**

October 2008